

# ወረርሽኝ ኤሌክትሪካዊ ጥቅማጥቅም ማስተላለፊያ (EBT)

## ዕድሜያቸው ከ 6 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች (2020-2021)

## በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች

ዘምኗል፡ ጁን 2021

## አጠቃላይ መረጃ

### 1. ዕድሜያቸው ከ 6 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት የወረርሽኝ EBT ፕሮግራም ምንድን ነው?

የወረርሽኝ EBT ፕሮግራም ወይም P-EBT በ 2020 - 21 የትምህርት ዘመን ባለመገኘት ወይም በልጆች እንክብካቤ ተቋማት መዘጋት ምክንያት የምግብ ወጪን ለመተካት ከ 6 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት የምግብ ጥቅሞችን ይሰጣል። እባክዎትን ለP-EBT የብቁነት መረጃ ከ5-11 ያሉትን ጥያቄዎችን ይመልከቱ።

### 2. በትምህርት ቤት ውስጥ ላሉት ልጆች ይህ ከ P-EBT እንዴት ይለያል?

በትምህርት ቤት ለተመዘገቡ ልጆች የ 2020-21 የትምህርት ዘመን የ P-EBT ፕሮግራም በት/ቤት ሪፖርት የተደረገው በአካል የመገኘት ውስንነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ዕድሜያቸው ከ 6 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት P-EBT በመሰረታዊ ምግብ መርሃግብር ላይ ያሉ ሁሉም ሕፃናት በልጆች እንክብካቤ ውስጥ ባለመገኘት ወይም በመዘጋታቸው ምክንያት ተጽዕኖ እንደደረሰባቸው ያስባል፡፡

### 3. የP-EBT ጥቅማጥቅሞችን ካገኘሁ፥ የስደተኝነት ሁኔታይን ይጎዳል ወይም ፐብልክ ቻርጅ ያድረገኝ ይሆን?

አይደለም። የፐብልክ ቻርጅ ለP-EBTጥቅማጥቅሞች ላይ አይተገበርም እንዲሁም P-EBTጥቅማጥቅሞች ስደተኝነት ሁኔታ ያለበትን ደረጃ አይጎዱም። ይህ በዋሽንግተን መንግሥት በሚደገፈው የምግብ ድጋፍ መርሃግብር በኩል P-EBT ን የሚቀበሉ ሕፃናትን ያጠቃልላል።

### 4. ልጄ በትምህርት ቤት ወይም በ Headstart ወይም በ ECEAP ፕሮግራም ምሳዎች ያገኛል፡፡ አሁንም ቢሆን ለP-EBT ብቁ እሆናለሁ?

አዎ፡፡ የP-EBTጥቅማጥቅሞች ተጨማሪ የምግብ ጥቅማጥቅሞች ናቸው። ልጆች የ P-EBTጥቅማጥቅሞች እየወሰዱ ቢሆንም በትምህርት ቤት ወይም በህብረተሰብ ቦታዎች ምግብ ተቀብሎ በመሄድ ሊቀጥሉ ይችላሉ ወይም በህዝብ ቦታዎች የሚሰጡ የኮቪድ-19 አስቸኳይ መመገቢያ ቦታዎች አስቸኳይ ምግብ መውሰድ መቀጥል ይችላሉ።

*ይህ ተቋም ለሁሉም እኩል ዕድል የሚሰጥ አገልግሎት አቅራቢ ነው።*

Washington State
Department of Social & Health Services
Transforming lives
(6/21)

## 5. ዕድሜያቸው ከ 6 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት P-EBT ማን ብቁ ነው?

መሠረታዊ ምግብን የሚቀበሉ ልጆች የሚከተሉትን ከሆኑ ለ P-EBT ብቁ ይሆናሉ:

- ዕድሜው ከ 6 ዓመት በታች ከሆነ።።
- ከኦክቶበር 1/2020 እስከ ጁን 30/2021 ባለው በማንኛውም ጊዜ ውስጥ በዋሽንግተን ግዛት መሠረታዊ የምግብ ዕርዳታ መርሃግብር የታቀፈ የቤተሰብ አባል ከሆነ።
- በብሔራዊ ትምህርት ቤት ምሳ ፕሮግራም እና በት/ቤት ቁርስ ፕሮግራም ውስጥ የሚሳተፍ በቦታው ላይ የምግብ አገልግሎት ውስንነት ያለው ትምህርት ቤት ያለበት ወረዳ ውስጥ የሚኖር ከሆነ።

## 6. በምግብ እርዳታ ላይ ነበርን ግን ጉዳዩ ተዘግቷል። ለ P-EBT አሁንም ብቁ ነን?

ለ P-EBT ብቁ የሆኑት ዕድሜያቸው ከ 6 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ቤተሰባቸው ከኦክቶበር 2020 እስከ ጁን 2021 ባለው መሠረታዊ ምግብ ላይ ከተካተቱ ለ P-EBT ብቻ ብቁ ይሆናሉ፤ በአውራጃቸው ውስጥ አንድ ትምህርት ቤት በቦታው ላይ የምግብ አገልግሎት ውስን ከሆነ። እንደገና ለማመልከት ፍላጎት ያላቸው ቤተሰቦች በ 877-501-2233 የ DSHS የደንበኞች አገልግሎት ማዕከልን ማግኘት ይችላሉ እንዲሁም በስልክ ማመልከት ወይም www.washingtonconnection.org ላይ ማመልከቻ ያስገቡ።።

## 7. አስቀድሜ የምግብ ድጋፍ አግኝቻለሁ። ለP-EBT ወዲያውኑ ብቁ እሆናለሁ?

በቁጥር 5 ላይ እንደተገለጸው ቢያንስ በቦታው ላይ የምግብ አገልግሎት ውስንነት ያው አንድ ትምህርት ቤት ባለው ወረዳ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ በራስ-ሰር የ P-EBT ጥቅምን ሊያገኙ ይችላሉ። ውስን የትምህርት ቤት ምግቦችን ተሞክሮ በሌላቸው ወረዳ ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦች ለ P-EBT ጥቅሞች ብቁ አይሆኑም።

## 8. ልጄ በልጆች እንክብካቤ ውስጥ ነው ፣ ግን እኛ በመሰረታዊ ምግብ መርሀግብር አንታቀፍም። ዕድሜያቸው ከ 6 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት P-EBT ብቁ ነን?

አይ። ዕድሜያቸው ከ 6 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት P-EBT ጥቅሞች የሚሰጡት በኦክቶበር 2020 እና ጁን 2021 መካከል መሠረታዊ ምግብ በሚቀበሉ ቤተሰቦች ውስጥ ለነበሩ ልጆች ብቻ ነው። ለመሠረታዊ ምግብ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ ብለው የሚያምኑ ከሆነ በ 877-501-2233 የ DSHS የደንበኞች አገልግሎት ግንኙነት ማዕከልን በማነጋገር በስልክ ማመልከት ወይም በ www.washingtonconnection.org ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ።

## 9. ልጄ ለ P-EBT ጥቅሞች ብቁ መሆኑን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

ብቁ የሆኑ ልጆች ማስታወቅያ የሚደርሳቸው ሲሆን ስማቸው የተፃፈበት የP-EBT ካርድ ይሰጣቸዋል። ብቁ ለሆኑት ልጆች ማስታወቂያው ከጁላይ 2021 መጨረሻ ጀምሮ ይላካል ብለን እንገምታለን። የ P-EBT ካርድ ገና ከሌላቸው ብዙም ሳይቆይ በፖስታ ይላካል። የፌዴራል COVID-19 የህዝብ ጤና ድንገተኛ ሁኔታ ከቀጠለ ተጨማሪ የ P-EBT ጥቅሞች በኋላ ሊጫኑ ስለሚችሉ ቤተሰቦች የ P-EBT ካርዶቻቸውን መያዝ አለባቸው። የ P-EBT ጥቅሞች አሁን ባሉ Quest EBT ካርዶች ላይ አይታከሉም።

## 10. የP-EBT ጥቅምን ለመውሰድ ለምን እንደዚህ ረጅም ጊዜ ይወስዳል?

የፌዴራል ሕግ ግዛቶች ቀድሞውኑ የ P-EBT ጥቅማጥቅሞችን ለተቀበሉ ልጆች ጥቅማ ጥቅሞችን እንዳይደገሙ ያስገድዳል። ትክክለኛ የጥቅማጥቅሞችን መጠን እንዲያገኙ በ Headstart ወይም በ ECEAP ፕሮግራሞች የተመዘገቡ ተማሪዎችን እንገመግማለን።

# የP-EBT ጥቅማጥቅሞችን ማግኘት

## 11. ዕድሜያቸው ከ 6 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት የ P-EBT ጥቅሞችን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

ብቁ የሆኑ ቤተሰቦች የP-EBT ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ማመልከት አይጠበቅባቸውም። እያንዳንዱ ብቁ የሆነ ልጅ ከ DSHS ጋር በመሰረታዊ ምግብ ጉዳያቸው በተዘገበው አድራሻ በቀጥታ በፖስታ የሚላክ የ P-EBT ካርድ ይቀበላል፡፡

## 12. ቀድሞውኑ የ P-EBT ጥቅሞችን አግኝተናል፡፡ የበለጠ እናገኛለን?

ልጆች ለነፃ ወይም ለቅናሽ ምግብ ብቁ ስለሆኑ ቀድሞውኑ የ P-EBT ካርድ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የተደገሙ የ P-EBT ጥቅሞችን መስጠት አልቻልንም ፤ ነገር ግን ህጻኑ ከ 6 አመት በታች እንደሆነ ህፃን የበለጠ ጥቅማጥቅሞችን ማግኘት እንደነበረበት ጉዳዩን እንገመግማለን፡፡ ለተጨማሪ ብቁ ከሆኑ ተጨማሪ ጥቅማጥቅሞች በተመሳሳይ የ P-EBT ካርድ ላይ ይቀመጣሉ።

## 13. ጥቅማጥቅሞቹ ወደ ትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ (ሴፕቴምበር 2020) ተመልሰው እንደገና ይመዘገባሉ?

አይ፡፡እኛ በመሰረታዊ ምግብ ቤተሰብ ውስጥ ላሉት ልጆች የ P-EBT ጥቅማጥቅሞችን መስጠት የምንችለው ህፃኑ ከኦክቶበር 1/2020 እስከ ጁን 30/2021 ባለው በመሠረታዊ የምግብ ድጋፍ ክፍል ውስጥ ለታቀፈበት ወራት ነው፤ በፌዴራል ምክር ቤት እንደፀደቀው፡፡

## 14. አድሱ የP-EBT ካርድ በመልዕክት ከደረሰ ምን ማድረግ አለብኝ (እስካሁን ከሌለኝ)?

ከP-EBT ካርድዎ ጋር የመጣውን መመሪያዎች ይከተሉና አስተማማኝ የግል መለያ ቁጥር ወይም ፒን ይፍጠሩለት። ካርድዎን ያስቀምጡ! የ P-EBT ፕሮግራም ከቀጠለ በመለያዎ እና በካርድዎ ላይ ተጨማሪ ጥቅሞችን ልንጨምር እንችል ይሆናል።

## 15. የP-EBT ካርዴን ማስቀመጥ አለብኝ?

አዎ፡፡ ተጨማሪ ጥቅማጥቅሞች በዓመቱ መጨረሻ ላይ ይሰጡ ይሆናል። ካርዶች ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ መቀጥ አለባቸው።

## 16. በእኔ እና አብሮ-ወላጅ መካከል አሳዳጊነትን ተከፋፍያለሁ፡፡ የልጆቻችንን P-EBT ካርድ ማን ሊጠቀም ይችላል?

እንደ አብሮ ወላጅ ወይም ተንከባካቢው ኃላፊነት ያለው የቤተሰብ አባል ብቁ የሆነውን ልጅ ወክሎ ጥቅሞቹን እስከወሰደ ድረስ ፤አብሮ ወላጆች እና ተንከባካቢዎች የልጁን P-EBT ካርድ እንዲጠቀሙ ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል።

## 17. ጥዬው ወይም አበላሽቸው ለP-EBT ካርድ ምትክ የምፈልግ ከሆነስ ምን ይሆናል?

P-EBTካርዶችን መተካት የEBT ሻጭ FIS ጋር በ 888-328-9271 በመደወል ይሰራል። ካርድ መተካቱ ካስፈለገ ቤተሰቦች www.ebtEdge.com ወይም የebtEdge appን መጎብኘት ይችላሉ። የP-EBT ካርድን ለመተካት ለመጠየቅ፥ የሚከተሉት መረጃዎች ያስፈልጎታል፡ የልጁ ሙሉ ስም፥ የልደት ቀን፥ ዚፕ ኮድ እና ሙሉ አድራሻ። የሚተካውን ካርድ ለመላክ የመልክት አድራሻው በሲስተም ውስጥ ካለው ጋር መመሳሰል አለበት። ካድዎን ለመቀበል እባክዎትን ከሰባት እስከ 10 የስራ ቀናት ይጠብቁ። አድራሻዎ EBT ሻጭ፥ FIS፥ በፋይሉ ላይ ካለው ጋር በማይመሳሰልበት ጊዜ ለተጨማሪ መረጃ ጥያቄ 27ን ይመለከቱ።

## 18. እነዚህን ጥቅማጥቅሞች ባሉኝ የምግብ EBT ካርዬ ላይ ማስቀመጥ እችላለሁ?

አይደለም። የP-EBT ፕሮግራም ለየት ያለ ነውና በ Quest EBT ካርድዎ ላይ ካሉ ጥቅማጥቅሞቹ ከሌላ ምግብ ወይም የካሽ ጥቅማጥቅሞች የተለዩ ናቸው።

## 19. ማስታወቂያ አላገኘሁም። ለ P-EBT ብቁ ነኝ?

ማስታወቂያ ካላገኙ ልጅዎ ብቁ ላይሆን ይችላል። ይህ ስህተት ነው ብለው ካመኑ እባክዎ ብቁ መሆንዎን ለማጣራት የ P-EBT የእውቂያ ማዕከልን በ 833-518-0282 ያነጋግሩ።

## 20. እነዚህን ጥቅማጥቅሞች አንፈልጋቸውም። ልተዋቸው እችላለሁ?

P-EBTን ለማግኘት ብቁ መሆናቸው የተወሰኑ ቤተሰቦች ጥቅማጥቅሞቹን ለቤተሰባቸው ለመጠቀምና የአከባቢው ኢኮኖሚ እንዲያድ እንዲያደርጉ እናበረታታለን። ጥቅማጥቅሞቹ የማይተላለፉ ስለሆኑ መስጠት ወይም መለገስ አይቻልም። አንደዚያም ሆኖ ጥቅማጥቅሞቹን ለመተው ከፈለጉ፥ ካረዱን ማበላሸት ወይም በካርዱ ጀርባ ላይ ባለው አድራሻ መመለስ ይችላሉ። ጥቅማጥቅሞች ጥቅም ላይ ሳይውል ከቆየ ከ274 ቀናት በኋላ ወዲያውኑ ይጠፋል።

# የP-EBT ጥቅማጥቅሞች መጠን

## 21. ልጁ ዕድሜያቸው ከ 6 ዓመት በታች በሆኑ የ P-EBT ሕፃናት ውስጥ ምን ያህል ያገኛል?

የምግቦች በጀት የሚወጣው የትምህርት ቤት የሥራ ሰዓቶች በ $ 6.82 በየቀኑ በ P-EBT መጠን በማየት ነው። ይህ በወር በአማካኝ በ 18 የሥራ ቀናት ተባዝቶ ምሳ ፣ ቁርስ እና መክሰስ ይሸፍናል። በቦታው ላይ የምግብ አገልግሎት ውስንነትን በተመለከተ በትምህርት ቤቶች የተዘገበውን መረጃ በመጠቀም የ P-EBT ጥቅማጥቅሙ መጠን በመሰረታዊ የምግብ ጉዳይ ላይ እንደተመለከተው በልጁ የመኖሪያ ክልል እና ከኦክቶበር 2020 እስከ ጁን 2021 በየወሩ በካውንቲው ውስጥ ሪፖርት የተደረገው ዝቅተኛው የምግብ አገልግሎት ላይ የተመሠረተ ነው። ጥቅሞች ከወረዳ ወረዳ ሊለያዩ ይችላሉ።

| የካውንቲ በጣም ብዙ ምግብ አገልግሎት | ስሌት | ዶላር መጠን በየወሩ |
|---|---|---|
| ሙሉ የርቀት ትምህርት ወይም የትምህርት ቤት መዘጋት | $6.82 x 18 x 100% | $123 |
| አንድ ቀን በአካል ወይም ሁለት ቀን በአካል | $6.82 x 18 x 70% | $76 |
| ሶስት ቀናት በአካል ወይም በአራት ቀናት በአካል | $6.82 x 18 x 30% | $37 |

## 22. መጠኑ ለምን በልጁ ትክክለኛ በልጆች እንክብካቤ ማዕከል መገኘት ላይ አይመሰረትም?

አብዛኛውን ልጆች ለመርዳት፥ ለልጆች የሚሰጠውን ሀገር-አቀፍ ደረጃ መጥን ተግባራዊ አድርገናል። የእያንዳንዱነት ተማሪ ተሳትፎ መከታተል አልቻልንም። ውስን ሰዓታት እና በልጆች እንክብካቤ ውስጥ ላሉት ልጆች መገኘትን ለመገመት የትምህርት ቤት ምግብ አገልግሎት አቅርቦትን እየተጠቀምን ነው።

## 23. የP-EBT ጥቅማጥቅም መጠን ሊለወጥ ወይም ሊስተካከል ይችላል?

የ P-EBT ጥቅማጥቅሞች መጠን በመሰረታዊ ምግብ ጉዳይዎ ውስጥ በተዘረዘረው በጣም የቅርብ ጊዜውን የክልል አውራጃ እና በዚያ ወረዳ ውስጥ ባሉ ት / ቤቶች ሪፖርት ባደረገው ዝቅተኛ የምግብ አገልግሎት ላይ የተመሠረተ ይሆናል። የልጅዎን የብቁነት ማስታወቂያ ሲቀበሉ በልጅዎ P-EBT መጠን ላይ ስህተት አለ ብነው ካመኑ፥ ብቁ መሆንዎን እንደገና እንዲያኡ ለመጠየቅ ወደ ጥሪ መዕከሉ በ 833-518-0282 መደወል ይችላሉ።

## 24. ተጨማሪ የP-EBT ጥቅማጥቅሞች ይኖራሉ?

የፌዴራል COVID-19 የህዝብ ጤና ድንገተኛ ሁኔታ እስካለ ድረስ የ P-EBT መርሃግብር ሊቀጥል ይችላል። ይህ እስከ ሰመር ወራት ድረስ ሊያካትት ይችላል። ለወደፊት ሊኖር ለሚችለው ጥቅአጥቅሞች ካርድዎን ማስቀመጥዎን እርግጠኛ ይሁኑ። ለተጨማሪ ዝርዝር ይህንን www.dshs.wa.gov/pebt የጎብኙ።

## የP-EBT ጥሪ ማዕከል

### 25. ለP-EBT ጥያቄዎች ለማን ልደውል?

ሁሉም የP-EBT ብቃት መስፈርት ጥያቄዎች ቀጥታ ለ P-EBT ጥሪ ማዕከል 833-518-0282 ማምራት ይችላሉ።

### 26. ፒኔን ለማስተካከል ለማን መደወል አለብኝ?

አንዴ የልጅዎን ካርድ ካገኙ ቤተሰቦች ፒን ለማዘጋጀት ለ EBT ሻጩ በ 888-328-9271 ሊደውሉ ይችላሉ::

### 27. በአድራሻ ለውጥ ምክንያት የP-EBT ሳልወስድ ከቀረሁ ማንን ማነጋገር እችላለሁ?

ለአድራሻ ለውጥ ድጋፍ ለማግኘት ቤተሰቦች በዚህ የ P-EBT ጥሪ ማዕከል ስልክ 833-518-0282 መደወል አለባቸው።

## የP-EBT ጥቅማጥቅሞችን መጠቀም

### 28. የP-EBT ጥቅማጥቅሞቼን የት መጠቀም እችላለሁ፥ ምንስ ሊገዛበት እችላለሁ?

የP-EBTካርድዎን እንዴ ዴቢት ካርድዎ ወይም Quest EBT ካርድዎ ይጠቀሙ? የP-EBT ጥቅማጥቅሞችዎ ከአብዛኛው የግሮሰሪ ማከማቻዎችና ገበሬዎች ምግብ መግዛት ይችላል። የP-EBT ጥቅማጥቅሞችዎን EBT በሚቀበሉ በማንኛውም የገበያ ቦታ ኦንላይን ጨምሮ EBT ከሚቀበሉት መጠቀም ይችላሉ። አብዛኛው ሱቆች EBT መቀበላቸውን የሚያሳይ ምልክት አላቸው። የP-EBT ጥቅማጥቅሞችዎ SNAP EBT ሊገዛ የሚችለውን ምግብ መግዛት ይችላሉ። EBT ከተዘጋጁና በትኩስ ከሚሸጡት ምግቦች ውጪ ለአብዛኛው ምግቦች ይሆናል። በEBT ማግኘት የሚቻለውን ምግም በበለጠ ለማወቅ ይህንን What can SNAP Buyመጎብኘት ይችላሉ

### 29. P-EBT ከፍራፍሬ እና ከአትክልቶች ማበረታቻዎች ጋር ሊያገለግል ይችላል?

አዎ:: ቤተሰቦች የ P-EBT ጥቅማቸውን ከተሳታፊ የፍራፍሬ እና የአትክልት ማበረታቻ ፕሮግራሞች ጋር መጠቀም ይችላሉ SNAP Market Match እና SNAP Produce Matchን ጨምሮ:: እነዚህ ፕሮግራሞች ቤተሰቦች በተሳታፊ የሸቀጣሸቀጥ መደብሮች እና በአርሶ አደሮች ገበያዎች ውስጥ የሚያገኟቸውን ብቃት ያላቸውን ፍራፍሬዎችና አትክልቶች እንዲጨምሩ ያስችላቸዋል:: የበለጠ ለማወቅ SNAP Match Programs::

### 30. በማገኛቸው ጊዜ ሁሉንም የP-EBTጥቅማጥቅሞችን መጠቀም አለብኝ?

አይደለም። ጥቅማጥቅሞች ከአንድ ወር ወደ ሌላ ወር ይተላለፋሉ። የP-EBTጥቅማጥቅሞችዎ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለመጨረሻ እስከሚጠቀሙበት ድረስ ለ274 ቀናት ከርድዎ ላይ የቆያል። የP-EBT ካርድዎን አይጣሉ። የኮቪድ -19 አስቸኳይ የህብረተሰብ ጤና እስካለ ድረስ፥ ተጨማሪ P-EBT ጥቅማጥቅሞችን በካርድዎ ላይ እንሰጣለን።

### 31. የኔን ፒን በP-EBT ካርዴ ላይ በተለየ ቀን ማስተካከል አለብኝ?

አንድ ካርድ ካልተሰካ እና ጥቅሞቹ ከተሰጠ በኋላ ባሉት 274 ቀናት ውስጥ ጥቅም ላይ ካልዋሉ ይወገዳሉ እና መተካት አይችሉም:: ቤተሰቦች ከርዱን እንደ ወሰዱ ፒናቸውን በP-EBT ጥቅማጥቅሞች ላይ እንዲያነቃቁ እናበረታታለን፥ ነገር ግን ፒንን ለማስተካከል ወይም P-EBT ከርድን ለማነቃቃት የተቀመጠ ቀነ-ገደብ የለም።

## 32. ያለኝን ቀሪ ሒሳብ እንዴት ማየት እችላሉ?

ያለዎትን ቀሪ ሒሳብ ለማወቅ ለEBT ሻጮች፥ FIS በ at 888-328-9271 መደወል ይችላሉ (በP-EBT ከርድ ጀርባ ላይ ያለው ቁጥር) ወይም እዚህ ይመልከቱ www.ebtEdge.com ወይም በስልክዎ ላይ የebtEdge መተግበሪያን ያውርዱ።

## 33. የሆነ ሰው ጥቅማጥቅሞችን ተጠቅሞታል። ልተካቸው እችላለሁ?

አይደለም። ማንኛውንም ጥቅም ላይ የዋለውን ጥቅማጥቀም መተካት አንችልም። አስተማማኝ የሆነና በቀላሉ ማስታወስ የሚቻለውን ነገር ግን በተለምዶ የሚጠቀሙትን ያልሆ ፒንን መምረጥ በጣም ጠቃሚ ነው። ካርድዎ ከጠፋ ወይም ከተሰረቀ ካርድዎን ሰርዘው ሌላ አድስ ለመጠየቅ የEBT ሻጭ፥ FIS በ888-328-9271 ላይ እንዲደውሉ እናበረታታለን። ማጭበርበር መኖሩን ከተጠራጠሩ፥ በዋሽንግተን ስቴት ዌልፌር ማጭበርበር መስመርን 800-562-6906 ላይ ይደውሉ።

# ሌላ የP-EBT መረጃ

## 34. ከአሁን በኋላ በምግብ ዕርዳታ ላይ አይደለሁም ፣ ግን ከቤተሰቤ ውስጥ ከ 6 በታች የሆነ ልጅ አለኝ እንደገና ማመልከት አለብኝ?

ተጨማሪ የምግብ እርዳታ ወይም የገንዘብ ድገፍ የሚፈልጉ ከሆነ፥ የማህበራዊና ጤና አገልግሎቶች መምሪያን በዚህ ደውለው 877-501-2233 ማግኘት ይችላሉ ወይም ይህነን የጎብኙ www.washingtonconnection.org:: ቤተሰቦችዎ ለመሠረታዊ የምግብ ድጋፍ ብቁ እንደሆኑ ከተረጋገጠ የ P-EBT ጥቅማጥቅሞች በተናጠል ይገመገማሉ።

## 35. በአሁኑ ጊዜ ሌሎች የምግብ ጥቅማጥቅሞች ይኖራሉ?

- USDA ሰመር ምግብ መፈለጊያ መሳሪያ ቤተሰቦች ለልጆች ምግብ የሚያቀርቡትን ቦታዎች ለማግኘት ሊረዳ ይችላል። በዚህ የምግብ አገልግሎቶች መሳተፍ ብቁ የሆኑትን ልጆች የP-EBT ጥቅማጥቅሞች ከማኘት አያግዳቸውም። በምንም ትምህርት ቤት ይማሩ እነዚህ የምግብ ፕሮግራሞች ዕድሜያቸው 18 ዓመት ለሆኑት እና ከዚያም በታች ለሆኑት ሁሉም ልጆች ይኖራል። ቤተሰቦች በሰመር ወራት በአቅራቢያቸው የሚገኙ ቦታዎችን ለማግኘት 1-866-3-HUNGRY (1-866-348-6479) ወይም 1-877-8-HAMBRE (1-877-842-6273) ደውለው መጠየቅ ይችላሉ::
- ለመሰረታዊ የምግብ ጥቅማጥቅሞች ለማመልከትይህንን www.washingtonconnection.orgማየት ይችላሉ።
- አዲስ ልጆች ካለዎት ለሴቶች፥ አዲስ ለተወለዱት ጨቅላ ህፃናት እና ልጆች ወይም ዕድሜያቸው እስከ 5 ዓመት የሆኑ ልጆችና ነብሰ-ጡር እናቶች እንደዚሁም ደግሞ ጡት ለሚያጠቡት እናቶች የምግብ ድጋፍ የሚያቀርበው ለWIC ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ተጨማሪ መረጃ በዚህ ያገኛሉ https://www.doh.wa.gov/YouandYourFamily/WIC።